# ቅዱስ ፍሬምናጦስ ከሣቴ ብርሃን

ኢትዮጵያ ሀገራችን ክርስትናን የተቀበለችው በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ሲሆን በሲኖዶስ ሕግ የኤጲስ ቆጶሳት መንበር ያገኘችው ግን በ4ኛው መ/ክ/ዘ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊው ሩፊኖስ ይህንኑ ታሪክ ሲዘግበው እንዲህ ይላል፡- ‹‹ሜሮጵዮስ የተባለ ነጋዴ (ፈላስፋ) ከሁለት ወጣት ዘመዶቹ ጋር በመሆን ከጢሮስ ተነሥቶ ወደ ሕንድ አቅጣጫ በጀልባ ጉዞ ጀመረ፡፡ እነዚህ ሁለት ወጣቶች ትልቁ ፍሬምናጦስ ታናሹ ደግሞ ኤዴስዮስ ይባላሉ፡፡ ይህ ክርስቲያን ሰው እነዚህን ወጣቶች አስከትሎ ወደ አፍሪካ የባሕር ጠረፍ በመምጣት በቀይ ባሕር ወደብ ውኃ ለመጠጣትና እግረ መንገዱንም ሀገር ለማየት ጀልባውን ጠረፍ ላይ አቆመ፡፡ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሰዎች (የአዱሊስ ነዋሪዎች) በጀልባዋ ላይ አደጋ በመጣል ሜሮጵዮስንና የጀልባዋን ቀዛፊዎች እዚያው ገድለው ሀብታቸውን ዘረፉዋቸው፡፡

ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ በማያውቁት ሀገር ያለ ሀብት ብቻቸውን በመቅረታቸው እያዘኑና እያለቀሱ ከዛፍ ሥር ተቀምጠው ይጸልዩ ጀመር፡፡ እነዚህን ወጣቶች በማየታቸው የተገረሙት መንገደኞች ከዚያ ቦታ አንሥተው ለአኵስሙ ንጉሥ ምርኮ አመጣንልህ በማለት አስረከቡዋቸው፡፡ ንጉሥ ታዜር (ኢዛና) በአኵሱም ቤተ መንግሥት ያድጉ ዘንድ ፈቃዱ ስለሆነ ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ ከታዜር ልጆች አብርሃና አጽብሐ ጋር አንድ ላይ አደጉ፡፡ በአእምሮ መብሰላቸውን በጥበብ ማደጋቸውን የተመለከተው ንጉሥ ታዜር ፍሬምናጦስን በጅሮንድ ኤዴስዮስን ደግሞ ጋሻ ጃግሬው አድርጎ ሾማቸው፡፡

ንጉሡ ሲያርፍ ሁለቱ ወጣቶች ሑር (ነፃ) ስለተለቀቁ ወደ ሀገራቸው ለመሄድ ሲነሡ መንግሥቱን በሞግዚትነት የተረከበችው ንግሥት አሕየዋ አብርሃና አጽብሐ (ኢዛናና ሳይዛና) አድገው ዙፋኑን እስኪረከቡዋት ድረስ በአስተዳደር እንዲረዱዋት ስለለመነቻቸው መሄዳቸውን ትተው በአማካሪነት ሲያገለግሏት ቆዩ፡፡

ፍሬምናጦስ ለክርስትና እምነቱ ቀናዒ ስለነበረ አስቀድሞ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ተሰብኮ በአኵስምና አካባቢዋ የነበረው የክርስትና እምነት የሚስፋፋበትን መንገድ ዘወትር ያስብ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሃይማኖት ብቻ እንጂ ክህነት፣ ቁርባን፣ ወዘተ. ስላልነበራቸው ያዝኑ እንደነበር ተመለከተ፡፡

ፍሬምናጦስ፣ አብርሃና አጽብሐ መንበሩን ሲረከቡ አስቀድመው አብረው በማደጋቸው በወንድምነት ያነሳሳቸውና የተማረውን ያስተምራቸው የነበረውን ጉዳይ አሳሰባቸው። አብርሃና አጽብሐ ባይጠመቁም እንኳን የፍሬምናጦስ ስብከት ስቧቸው የነቢያት ትንቢት ተፈጽሞላቸው በማየታቸውም ደስ ብሏቸው ክርስትናውን ተቀብለው ነበርና በጉዳዩ አጥብቀው በማሰብ ከፍሬምናጦስ ጋር ከተወያዩ በኋላ ለዚሁ ተግባር በዘመኑ የአፍሪካ የክርስትና ማዕከል ወደ ነበረችው እስክንድርያ ላኩት።

ፍሬምናጦስ እስክንድርያ የደረሰው አለ እስክንድሮስ አትናቴዎስን አስከትሎ ለጉባኤ ኒቂያ በወጣበት ጊዜ ነበርና እስኪመለሱ ድረስ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን እየተማረ በትዕግሥት መጠበቅ ግድ ሆነበት። እለ እስክንድሮስ በጉባዔ ነቂያ በአትናቴዎስ አፈጉባዔነት አርዮስን ረትቶ ከተመለሰ በኋላ ወዲያው ስላረፈ በመንበሩ አትናቴዎስ ተተካ። ፍሬምናጣስ የተላከበትን ዐቢይ ጉዳይ ለሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ አቀረበ። አትናቴዎስ ስለ ኢትዮጵውያን ሃይማኖት በሚገባ ከተረዳ በኋላ ለፍሬምናጦስ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን አስተምሮ ‹‹***ሌሊስ ቆጶስ ዘአኩሱም ወዘኵላ ኢትዮጵያ***›› ብሎ በቅብዓትና በአንብሮተ እድ ሹሞ ላከልን። ፍሬምናጦስ ጵጵስናውን ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ፣

1. የወንጌል ትምህርት በስፋት ለሕዝቡ የሚያዳርሱ፣ የሚያጠምቁና የሚያቆርቡ ካህናትንና ዲያቆናትን ሾመ።
2. በአብርሃ አጽብሐ አማካኝነት አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን አሳነፀ።
3. በዘመኑ የኢትዮጵያ ግዛት ወደ ነበሩት ኑብያ፣ አኑኖእና መርዌ አምስት ቆምሳትን በመላክ ትምህርተ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን እንድትስፋፋ እንዲሰበክ አድርጓል።
4. ቅዱሳት መጻሕፍት ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥና ከግሪክ ወደ ግእዝ እንዲተረጎሙ አድርጓል።
5. የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ በመለወጥ ከግራ ወደቀኝ የመጻፍንና የማንበብን ዘዴ ያስተማረው እርሱ ነው።

በዚህም መሠረት ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ በ350 ዓ.ም እንዲታወጅ አድርጓል። ኢትዮጵያውያን ይህንን ታላቅ አባት በሃይማኖቱና በምግባሩ ስለወደዱት «አቡነ» (አባታችን) የሚለውን ማዕረግ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጡት ለርሱ ነው። በብርሃናዊው ሥራውም «**ከሣቴ ብርሃን-*ብርሃን ገላጭ***› ብለውታል።

አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተባለው ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ክርስትና እንዲስፋፋ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ በመውጣትና በመውረድ የሚገባውን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ሐምሌ 26 ቀን ዐረፈ።

ይህ ታላቅ አባት የኢትዮጵያውያን ባለውለታ፣ የወንጌልን ፋና ይበልጥ እንዲበራ ያደረገ፣ መንበረ ጵጵስናን ያስገኘልን፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ለኢትዮጵያ የወጠነልን እና አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን ያስተከለልን ነውና ዘወትር ልናስበው በዓሉንም ልናከብርለት ይገባል፡፡ ሥዕሉም ከየቤታችን ሊጠፋ አይገባም፡፡

የሚያሳዝነው ግን ቤተ ክርስቲያኑ በሚገኝበት ትግራይ ውስጥ ካልሆነ በቀር በአብዛኛው የሃገራችን ክፍል በዓሉ እምብዛም ትኩረት አለመሰጠቱ ነው፡፡ በአዲስ አበባም ሆነ በታላላቅ ከተሞች በስሙ የሚጠራ አንድ ቤተ ክርስቲያን መጥፋቱ በታሪክም በእግዚአብሔርም የሚያስወቅሰን ነገር ነው፡፡

ኤፍ.ጂ. ሆልዊክ የተሰኘው ጸሐፊ (Louisiana) (በዩናይትድ ስቴት ግዛት) በ1787 ዓ.ም እ.ኤ.አ የአካባቢው ሰዎች በከፍተኛ ድምቀት የቅዱስ ፍሬምናጦስን በዓል ሲያከብሩ መመልከቱና እነርሱም ከዚህ ከአፍሪካ በባርነት የሄዱ ጥቁሮች መሆናቸውን ማረጋገጡን ጽፎ ነበር፡፡ የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው ይሏል ይኼ ነው፡፡ እኛ ስንረሳው እነርሱ ግን መኩሪያቸው ነውና ዘወትር ያከብሩታል፡፡

ሌላው የሚያሳዝነው ነገር የሮማ ቤተ ክርስቲያን በኦክቶበር 27፣ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በኖቬምበር 30 በዓሉን ሲያከብሩለት የሾመችውና የላከችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ግን ፈፅማ ከበዓላት ቀኖናዋ ማውጣቷ ነው፡፡ ይህ ግን ለምን ይሆን? አቡሰ ሰላማ የቀደሰበት በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ቅዳሴና የባረከበት የእጅ መስቀሉ ዛሬም በተድባበ ማርያም ቤተክርስቲያን ይገኛል፡፡ ጸሎቱና በረከቱ በኛ ላይ ይደርብን፡፡ አሜን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

---

**ምንጭ**


History ECCLP.L ,,I 478-80

Butler's Lives of the Saints vol. iv, London 1956, p.209.

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 23-27፡፡

ትንሣኤ ቁ.60/75፣ገጽ 23 ትንሣኤ ቁ.83/76፣ ገጽ 3

Sergew H/Sellassie; Ancient & Medieval Ethiopian History to 1270 AA.p.104)